# የሦስቱ አገራት ፍሪያማ ውይይት

**ተስፋዬ ለማ 12/31/13**

የሕዳሴው ግድብ ግንባታ የጋራ ተጠቃሚነት ላይ መመስረቱን ሱዳን ከተገነዘበች ወራት አልፈዋል። ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር ተባብራ ለመስራት ዝግጁ መሆኗንም በተለያዩ አጋጣሚዎች አስታውቃለች።

የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ ተመስርቶ እንደሚካሄድ የሱዳን ሕዝብና መንግሥት መገንዘባቸውን ተከትሎ ግብጽ ላይ የነበረው ጥርጣሬ እንዲወገድም መንግስት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ አጠቃቀም ዙሪያ ከሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት ጋር በፍትሃዊና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ መርህ ትከተላለች። ግብፅም የግድቡን ግንባታ በዚህ መልኩ እንድትገነዘበው የኢትዮጵያ ፍላጎት እንደሆነም ይታወቃል።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ያለው ሁለንተናዊ ግንኙነት እየተጠናከረ መጥቷል። ሁለቱ አገራት በቅርቡ 13 ሥምምነቶችን ተፈራርመዋል። አገራቱ ወደፊትም ጋር በጋራ ጉዳዮች ዙሪያ በቅርበት ለመሥራት ያላቸውን ፍላጎት ያሳያል።

በቅርቡ ካርቱም ውስጥ በታላቁ የሕዳሴ ግድብ ዙሪያ በተካሄደው የኢትዮጵያ፣ የሱዳንና የግብጽ የሦስትዮሽ የሚኒስትሮች ስብሰባ ላይም በሦስት ዓበይት ጉዮች ላይ መግባባት መደረሱ ትልቅ እመርታ አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

በተለይ በታላቁ የህዳሴ ግድብ ላይ በዓለም አቀፍ የኤክስፐርቶች ቡድን ባቀረበው ምክረ ሃሳብ አፈጻጸም ላይ ለመምከር በሚቋቋመው የሦስትዮሽ ኮሚቴ ላይ የአባላት

ስብጥር፣ ዓላማ፣ ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ መግባባት ላይ መደረሱ ለሦስቱም አገራትና ህዝቦች መልካም ነገር እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ ሰሞኑን በኩዌት በተካሄደው የአረብ አገራት ስብሰባሳይ በተካፈሉበት ወቅት የተለያዩ አገራት መሪዎች ጋር መወያየታቸው ይታወሳል።

ከእነዚህ አገራት መካከልም የግብጹ ጊዜያዊ ፕሬዚዳንት አደሊ መንሱር ይገኙበታል። ሁለቱ አገራት ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ እየገነባች ባለው የህዳሴው ግድብ ዙሪያ ውይይት ከጀመሩ ቆይተዋል። ሁለቱ መሪዎች በነበራቸው ቆይታ በናይል ወንዝ ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀምና እየተገነባ ባለው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ ተነጋግረዋል። ግንባታው እየተፋጠነ ያለው ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ በተፋሰሱ የግርጌ አገራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሌለው በዓለም ዓቀፍ የመስኩ ባለሙያዎች ከቀረበው ሪፖርት ባሻገር በአገራት መካከል የጠነከረ የመተማመን መንፈስ ለማዳበር በቅርበት መስራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መክረዋል።

ኢትዮጵያ እየገነባችው ያለው የህዳሴው ግድብ ግብጽን የሚጎዳ አለመሆኑ በተገቢው መንገድ ግብጻዊያን እንዲረዱት ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች። ባለፈው ወር መጨረሻም የሦስቱ አገራት የውሃ ሚኒስትሮች በሱዳን ካርቱም ተገናኝተው መምከራቸው ይታወቃል። ዓለም አቀፉ የቴክኒካል ኮሚቴ ያቀረበው ሪፖርት አፈጻጸም ላይ ቢጋር የሚያወጣ ኮሚቴ ለማቋቋምም መስማማታቸው ይታወቃል።

ሁለቱ አገራት በጉዳዩ ዙሪያ በጥልቀት መምከር እንዲችሉም በኅዳር ወር ማብቂያ ላይ በሱዳን መዲና ካርቱም ውስጥ ተገናኝተው ለመነጋገር ተስማምተዋል።

ኢትዮጵያዊያን ለዘመናት ሲቆጩለት የኖሩት የአባይ ወንዝን ለልማት የማዋሉ ጉዳይ ምላሽ ያገኘው ታላቁ የኢትዩጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በተጀመረበት ወቅት እንደነበር የአደባባይ ምስጢር ነው።

በታላቁ የህዳሴ ግድብ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ ከዋዜት የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አመራሮችና በኃይማኖት ሽፋን ከሚንቀሳቀሱ የከሰሩ ፖለቲከኞች በስተቀር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከዳር ዳር በአንድ ድምጽ የተቀበለው የልማት ፕሮጀክት ነው። በመካከሉ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይኖረው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

ህዝቡ ገንዘቡን፣ ጉልበቱንና እውቀቱን አያፈሰሰበት ያለው ግድብ የህዳሴው ግድብ ሲጠናቀቅ ከኢትዮጵያ አልፎ የአካባቢውን አገራት ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ ይገመታል።

ገና ከአሁኑ እንኳን በኢትዮጵያ እየተካሄደ ባለው የኤሌክትሪክ ልማት ጎረቤት አገራት ሳይቀር ተጠቃሚ መሆን መቻላቸው መረጃዎች ያሳያሉ። ጅቡቲና ሱዳን ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት ጀምረዋል። ኬንያም አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያስችላት የኤሌክትሪካ ማስተላለፊያ መስመሮች እየተዘረጉ ይገኛሉ። ሌሎች የአካባቢው አገራትም በቀጣይ ከኢትዮጵያ ጋር በኢኮኖሚ የሚያስተሳስርና ተጠቃሚ የሚያደርግ ስራ እየተሰራ ይገኛል። የዚህ ሁሉ ማጠንጠኛው ደግሞ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ነው።

በኢትዮጵያዊያን በኩል ከተወሰኑ ድህነት ናፋቂዎችና የህዝብ ጠላቶች በስተቀር የፕሮጀክቱ ጠቀሜታ የማያጠያይቅ የጋራ ስምምነትን አግኝቷል። ፕሮጀክቱን ዳር ለማድረስ መላው ኢትዮጵያውያን በአንድ መንፈስና በአንድ አስተሳሰብና ተግባር በመነሳት ለግንባታው ስኬት እየሰሩ ይገኛሉ። ይህ በአንድ በኩል ለአገራቸው ልማት ያላቸውን ቁርጠኝነት ያስመሰከረ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን ልማት ለማይሹ ወገኖች የጽልመት ሕልማቸው እንደማይሳካ ያሳየ እንቅስቃሴ ሆኗል።

መንግስትም አገሪቱን ለማልማት እየገነባቸው ካሉት በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች መካከል ለዚህ ግድብ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በብሄራዊ ደረጃ ስራውን የሚከታተል ዐቢይ ኮሚቴ በማዋቀር ስራው እንዲፋጠን እያደረገ ያለበት ሁኔታ ይገኛል። በታላቁ ህዳሴ ግንባታ እስካሁን ድረስ ከተከናወኑ ዐበይት ተግባራት አንዱ የግድቡን የፍሰት አቅጣጫ የማስቀየር ስራ ነው። ይህ በግድቡ ግንባታ ሂደት ከሚኖሩ ትላልቅ አቅምንና ሙያን የሚጠይቁ ክንውኖች አንዱ እንደሆነ ይታወቃል። ይህ ከባድ ተግባር በስኬት ተጠናቋል።

ከዚህም በተጨማሪ ስራውን በታቀደለት ጊዜ ለማከናወን የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶች ተዘርግተዋል። ከዚሁ ጎን ለገን በአቅራቢያው አስፈላጊውን ግብአት ማቅረብ የሚችሉ የሁለት ፋብሪካዎች ተከላ ሙሉ በሙሉ ከመጠናቀቁም በላይ ከግድቡ ጋር ተያይዞ ሌሎች በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል።

የህዳሴው ግድብ 30 በመቶ በላይ የሚሆነው የግንባታ ክንውን ተጠናቋል። በጣም ፈታኝና ወሳኝ የሆነው የግድቡ የመሰረት ስራም በመገባደድ ላይ ነው። በመሆኑም ፕሮጀክቱን በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ርብርብ እየተደረገ ነው።

የታላቁ የህዳሴ ግድብ ጉዳይ የተፋሰሱ የታችኛው አገራት ሳይቀር ክትትል እየተደረገለት መሆኑን አንዳንድ ዘገባዎች ያሳያሉ። በሱዳን በኩል ያለው ሁኔታ ግልጽ ወጥቷል። አገሪቱ ከህዳሴው ግድብ ተጠቃሚ እንደምትሆን አውቃ አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ ጥረት እያደረገች ትገኛለች። በግብጽ በኩልም አብዛኛው ህዝብ ተመሳሳይ አመለካከት እንደሚኖረው ቢገትም አፍራሽ ሃሳብ የሚያራምዱ መኖራቸው አይካድም።

በግብጽ ሰላምና መረጋጋት ባይኖርም በየጊዜው የሚቀያየሩ አመራሮች የሕዳሴው ግድብ ዋና አጀንዳቸው እንደሆነ ሲገልጹ ይደመጣሉ። የግብጽ ባለስልጣናት የህዳሴውን ግድብ ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴ እያደረጉ ያሉት አንድም ህዝቡን ለማነሳሳት በሌላ በኩል ደግሞ ግድቡ ጉዳት ያደርስብናል በሚል እሳቤ ሊሆን እንደሚችል ብዙዎች ያምናሉ።

በአሁኑ ወቅት ኃላፊነት ላይ ያሉት አመራሮችም እንደቀደሙት ሁሉ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ከዋና ዋና አጀንዳዎቻቸው ቀዳሚውን ስፍራ የያዘ እንደሆነ ደጋግመው በመናገር ላይ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ መንግስት ከግብጽ ህዝብና መንግስት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር እንደሚፈልግ በተደጋጋሚ ጊዜ አስታውቋል። ኢትዮጵያ የግብጽን ህዝብ ሊጎዳ የሚችል ፕሮጀክት እንደማትገነባ በማስገንዘብ ጭምር።

በግብጽ ተፈጥሮ ያለው የእርስ በርስ ግጭትና ደም መፋሰስ ቆሞ በሰላማዊ መንገድ ሁሉን ህዝብ የወከለ መንግስት እንዲኖር የኢትዮጵያ ጽኑ ምኞት ነው። በአገራቱ ሠላም ሰፍኖ ሁለቱ አገራት በአባይ ተፋሰስ ላይ የሚያደርጉት የልማት ትብብር እንዲጠናከርና ሁለቱንም ሕዝቦች ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስል የተቀናጀ ልማትን እውን ለማድረግ የኢትዮጵያ ፍላጎት መሆኑ እሙን ነው።

ይሁንና በግብጽ በኩል ደግሞ ባለማወቅም ሆነ በእውቀት ላይ ተመስርቶ በጥቂት ግለሰቦች የሚነሳ ስጋት እንዳለ ይታወቃል። የግድቡ መገንባት ወደ ሱዳንና ግብጽ የሚፈሰውን የውሃ መጠን ይቀንሰዋል፤ ግድቡ በአጋጣሚ ቢናድ በውኃ እንጥለቀለቃለን የሚሉት ስጋቶች የሚጠቀሱ ናቸው።

እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ በህይወታቸው እያሉ በቂ ትንተና የሰጡበትና በአብዛኛው የግብጽ ህዝብ ዘንድም ተቀባይነት ያገኘ ሁኔታ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ አሁንም መነሳቱ አልቀረም።

አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ መንግስት ግብጽ ለምታነሳቸው ስጋቶች በቂ ማብራሪያ ለመስጠትም ሆነ ከግብጽ ጋር በተለያዩ የትብብር መድረኮች ለመወያየት ያለውን ዝግጁነት እየገለጸ ይገኛል።

በአገራቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በመተማመንና በሁለትዮሽ ጥቅም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ በኢትዮጵያ አነሳሽነትና ቀስቃሽነት ከሦስቱ

አገራት ከፍተኛ ባለሙያዎች ተውጣጥተው ከዓለም ሕብረተሰብም ታክሎባቸው የታላቁን የህዳሴ ግድብ ግንባታ ደረጃና ሊያመጣው የሚችል ችግር በገለልተኛ ዓለም አቀፍ ቡድን መጠናቱ ለአገራቱ ህዝቦች መተማመን የጎላ ፋይዳ ይኖረዋል ከሚል እምነት የተነሳ ነበር።

በዚህ መሰረት ከኢትዮጵያ፣ ከሱዳንና ከግብጽ የተውጣጣው ዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ቡድን የታላቁ ሕዳሴ ግድብን ላለፈው አንድ አመት ተከቶል አጥንቷል። ባለሙያዎቹ ያጠኑትን ጥናት ለሦስቱ አገራት መንግስታት አስረክበዋል።

ዓለም አቀፉ የባለሙያዎች ቡድን ያቀረበው ጥናት ላይ አንዳንድ ግብጻዊያን በስጋት ሲያነሷቸው የነበሩ ጥያቄዎችን ጭምር መልሷል። በሪፖርቱ መሰረትም ታላቁ የህዳሴው ግድብ ወደ ታችኛው የተፋሰሱ አገራት የሚፈሰውን የውኃ መጠን እንደማይቀንሰው አረጋግጧል።

ግድቡ ወደ ሱዳንና ግብጽ የሚፈሰውን ውኃ እንዲቀንስ ሊያደርገው ይችላልን? የሚለውን የስጋት ጥያቄ በማያሻማ ቋንቋ ጥናቱ መልሷል። እርግጥ ነው በወቅቱ ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ይህንን በሚመለከት በቂ ማብራሪያ ሰጥተውበት ነበር። የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝብ የግብጽን ሕዝብ ሊጎዳ የሚችል ምንም ዓይነት ልማት የማልማት ፍላጎት ጨርሶ የለውም። ይሁን እንጂ ጥናቱ ከወጣ በኋላም ቢሆን አንዳንድ ግለሰቦች የተሳሳተ ሃሰብ ሲያቀርቡ ይስተዋላሉ።

የአንዳንዶቹ አስተያየት ሰጪዎች ሃሳብ የሚመነጨው በታላቁ የህዳሴ ግድብ ላይ በቂ ጥናትና ምርምርን በማድረግና ያለውን ተጨባጭ ነገር በመረዳት ሳይሆን በበሬ ወለደ ዓይነት ወሬ ነው። የበሬ ወለደ ወሬ ቢሆንም ሕቡእ አጀንዳ እንዳለው ግን አያጠያይቅም። የሁለቱን አገራት ህዝቦችን ለማወክና በጥላቻ ቀለበት ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ ያለመ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል። አንዳንዶቹ ደግሞ ጉዳዩን ለሌላ የፖለቲካ ፍጆታ ለማዋል የሚሞክሩ መሆናቸውን ለመረዳት

አያዳግትም። ይህም ቢሆን በህዝቦቹ መካከል መቃቃርን የመፍጠር ዓላማ ያለው ነው።

ሆኖም ግን የኢትዮጵያና የግብጽ ህዝቦች በምንም መልኩ የማይፈቱ ሕዝቦች ናቸው። በመካከላቸወ ያለው ታሪካዊና ባህላዊ ትስስር በቀላሉ የሚፈለቀቅ አይደለም። እነዚህን ህዝቦች በጋራ ሊጠቅም የሚችል እንጂ አንዱን ወይም ደግሞ ሁለቱን ህዝቦች የሚጎዳ ፕሮጀክት እንደማይገነባ እሙን ነው። ምክንያቱም የአባይ ውሃ ለኢትዮጵያኖችም ሆነ ለግብጻዊያን ህይወታቸው ነው።

በአንድ በኩል ጉዳዩን ለሌላ ፍጆታ ለማዋል በሌላ መልኩ ደግሞ በተገቢው መንገድ ባለመረዳት የተነሳ ስጋት ቀጣይነት እንዳይኖረውና የግብፅ ሕዝብ በግላጭ እንዲያውቁው ለማድረግና አስተማማኝ መተማመንን በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ለመፍጠር ሲባል ነበር ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ቡድን ተቋቁሞ ግድቡ የሚያስከትለው ምንም ዓይነት ጉዳት እንደሌለው እንዲያረጋግጥ በማሰብ ሀሳቡን ያመነጩትና ከሦስቱ አገራትና ከሌላ ዓለም የተውጣጡ በዘርፉ ከፍተኛ እውቀትና ልምድ ያላቸው አባላት የተሰባሰቡበት ቴክኒካል ኮሚቴ እንዲመሰረትና ጥናቱን እንዲያደርግ የተደረገው።

የዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ቡድኑም በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ያቀረበው ጥናት የሚያሳየው ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ይገልጹት ከነበረው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነገር ነው። ይሁንና አሁንም ግብጽ ከስጋት ነፃ መሆን የቻለች አትመስልም፤ይልቁንም በተለያየ ጊዜ አጀንዳ እያደረገችው ትገኛለች። ከኢትዮጵያ ጋርም ለመወያየት ትፈልጋለች። ሁለቱ አገራት በቀጣዩ ወር ውይይት ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ለመሆኑ የህዳሴውን ግድበ አስመልክቶ በመጪው ወር በሁለቱ አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የሚደረገው ውይይት ምን ላይ ሊያተኩር ይችላል? የኢትዮጵያ መንግስት ከግብጽ ጋር ተያይዞ እያነሳችው ካሉት ዓበይት ጉዳዮች በግብጽ ሠላም እንዲፈጠርና የተረጋጋች አገር እንድትሆን የሚል ይገኝበታል። በግብጽ የተረጋጋ

መንግስት ሲኖር ሠላም ይኖራል፤ ሠላም በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለሁለቱ ህዝቦች ለማስረዳትና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱን ለማጠናከር ያግዛል። የግብጽ ህዝብ ኢትዮጵያ በአባይ ተፋሰስ እየገነባችው ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተጠቃሚ እንደሚሆን ለማስገንዘብም እንደሚያግዝ ይነገራል።

ለኢትዮጵያዊያንና ለግብጽ ሕዝቦች የሚጠቅም ግድብ እንደሆነና ሁለቱን ሕዝቦች በኢኮኖሚ የሚያስተሳስር መሆኑን በጥሞና እንዲገነዘቡ ያግዛል። ለዚህም ነው ኢትዮጵያ የግብፅም ሆነ የሌሎች አገራት ሠላም የራሷን ሠላም እንደሆነ አድርጋ የምታየው። በቀጠናው ባሉ አገራት የሚፈጠር አለመረጋጋትና ሁከትም ኢትዮጵያንም እንደሚጎዳ በመገንዘብ በአፍሪካ ሠላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ላይ የምትገኘው።

ባለፉት ውይይቶች መግባባት ላይ ባልተደረሰባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ለመነጋገር የሦስቱ ሀገራት የጋራ የሚኒስትሮች በታሕሳስ ወር ማብቂያ ላይ በካርቱም ይካሄዳል።
የህዳሴው ግድብ ወደ ግብጽና ሱዳን የሚፈሰውን የውሃ መጠን እንዲጨምር እንደሚያግዝም የባለሙያዎቹ ጥናት ያሳያሉ። አመቱን ሙሉ ተመሳሳይ የውሃ መጠን ማግኘት እንደሚችሉም በተደጋጋሚ ይገለፃል። እንግዲህ በመጪው ወር በሁለቱ አገራት የውሃ ሚኒስትሮች የሚደረገው ውይይት በህዳሴው ግድብ ግንባታ ማዘግየትም ሆነ የማምረት አቅሙን መቀነስ ጋር የተያያዘ ነገር አይኖርም።

ይህንን በሚመለከት ኢትዮጵያ ያላትን አቋም ያለማቅማማት አስታውቃለች። የታላቁ ህዳሴ ግንባታ ለአንድ ደቂቃም ቢሆን እንደማይዘገይ በተደጋጋሚ ገልጻለች። ከሚይዘው የውሃ መጠንና ከሚያመነጨው ሃይል አንፃርም ቢሆን ቀደም ሲል ከተያዘው እቅድ እንደማይቀንስ ተናግራለች። ግብፃውያን ከኢትዮጵያ ጋር የሚወያዩበት ጉዳይ ከእነዚህ ሁለት ነገሮች ውጭ እንደሚሆንም መገመት አያዳግትም። ግንባታውን ከማዘግየትና የምርት አቅሙን ከመቀነስ ውጭ ምን

ዓይነት የመወያያ ጉዳይ ሊኖር ይችላል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ አስፈላጊ ይሆናል።

ዓለም አቀፍ ቡድኑ የቀረበው ግንባታው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን የሚያሳየውና ወደ ታችኛው የተፋሰሱ አገራት የሚሄደውን የውሃ መጠን የማይቀንስ መሆኑን ያስቀመጠው ድምዳሜ ላይም የጋራ መግባባት ለመፍጠርም የሚያስችል ውይይት ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

በቀጣይም በሁለቱ አገራት የሚካሄደው ውይይት ውጤታማ ሆኖ የሁለቱም አገራት ህዝቦች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሰላማዊ መግባባትና የጋራ ልማት የሚያፋጥኑበት የትብብር ስምምነት ላይ ይደረሳል የሚል እምነት ያላቸው አስተያየት ሰጪዎች ሚዛን እየወሰዱ እንደሚገኙ መገመት ይቻላል። በዚህ መካከል ግን የግብፃውያን መረጋጋት ለዚህ ውይይትም ወሳኝነት  ይኖረዋል።